# ድንጋይን የሚያናግረዉ ውኃ ነው

## ክፍል-፪

እርግጥ ነዉ እንደሚባለዉም ድንጋይን የሚያናግረው ሲጓዝ ዉሎ ሲጓዝ የሚያድር ዉኃ ነው። እኔን ጠጠሩንም ሳይቀር ብቻዬን የሚያስተክዘኝ ይኸዉ ነው። በክፍል አንድ ለወፍ ላራዊቱ፤ ለሳር ለቅጠሉ፤ ሳይቀር የሚበቃዉን ፍትህ እነደ ጨርቅ በክንድና በስንዝር እየለኩ ጥቢቆ በመስፋት ለተወሰነ የሕብረተሰብ ክፍል እናላብሳለን የሚሉ "የቀይ፣ የቀይዳማ፣ የጠይም፣ የጥቁር ሕዝብ ወዘተ ነፃ አውጪዎች" ጠጠርን ሳይፈልግ አናግረዋል። ዛሬ ጠጠርን የሚያስተክዘው ጎርፍ ደግሞ ከቤተ-ክህነት ይነሳል።

ምእመናን ከቤተ-ክህነት የሚመኙትም ሆነ የሚጠብቁት የፅድቅ መገኛ መንገድን፣ ሰብአዊነትን፣ ሰላምን፣ እርቅን፣ የመንፈስ ልዕልና አርያነትን፣ የሥነ-ምግባር ምሳሌነትንና ሌሎችንም አለም ያላትን በጎ ነገሮች ነው። በለሙያዎች እንደሚሉት ማእበል የሚፈጠረው የተፈጥሮ ሚዛን ሲናጋ ነው። ከቤተ-ክህነት የሚመነጨው ጎርፍም መንስኤው ካህናት የተሸከሙት መስቀል፣ ቆብ፣ ማእረግ፣ ቃለ-መሐላ፣ አለባበሳቸውና ሌላውም ሌላምዉም ነገር ከግብራቸው ጋር አራባና ቆቦ ሆኖ አልገናኝ ሲል ነው። ይህ ችግር ስር የሰደደ መሆኑ እየታወቀ ብዙ ሰዉ ጉዳዩን ባደባባይ ሲያነሳ ብዙም አይታይም። ብሶቱ፣ ቁስሉ፣ ትዝብቱና ጭንቀቱ ግን ከአብዛኛው ምእመናን ፊት ላይ ተንቀልቅሎ ይታያል። እንኳን ፊትን ማንበብ ለሚያዉቀው ብዙም ለማይችለው ለኔ ቢጤውም ቢሆን ፍንትው ብሎ ይነበባል።

በመሐንዲሶች ወይም በሐኪሞች የሞራልና የሥነ-ምግባር ጉድለት ለመተቸት የግድ መሐንዲስ ወይም ሐኪም መሆን ኢያስፈልግም። የቤተ-ክህነትን የሞራል ማሽቆልቆል ለማንሳትም የግድ መሪጌታ፣ ቄስ፣ ዲያቆን፣ መነኩሴ ወይም ጳጳስ መሆን የሚያስፈልግ አይመስለኝም። ሙያዎች በጥበባዊ (ቴክኒካል) ባህሪያቸው ይለያዩ እንጂ ሞራላዊ ወይም ሥነ-ምግባራዉ ገፅታቸዉ ይመሳሰላል። የገበሬዉ፣ የመምህሩ፣ የመሐንዲሱ፣ የሾፌሩ፣ የጠበቃዉ፣ የዳኛው፣የሐኪሙ፣ የካህኑ፣ የነጋዴው፣ ወዘተ ሁሉ የሞራል ግዴታ ለሰው ልጅ በጎ ነገር መስራትና ክፉ ነገርን ሁሉ ማስወገድ፤ የሥነ-ምግባር መርሆዉም በሥራ ብቁ ሆኖ መገኘት፣ አለመቅጠፍ፣ በመቅቡጥ አለመደለል፣ ለፍትህ መስፈን አስተዋጽኦ ማድረግ የመሳሰሉት ናቸው። የሃይማኖት መሪዎች በተለይም የክርስትና መሪዎች የእየሱስን መንገድ ለራሳቸው ብቻ መከተል፤ የእስልምና መሪዎችም የመሐመድን ፈለግ መከተል ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም በዚሁ ረድፍ የማሰልፍ የሙያም ሆነ የቃለ-መሐላ ግዴታ እንዳለባቸው አምናለሁ። ከክርስቶስ ልደት በፊትም ሆነ በኋላ እንደዚህ አይነቱን የሃይማኖት ግዴታ እየተወጡ ያለፉ ነቢያትም ሆነ ሐዋሪያት አያሌ ናቸዉ።

ብዙዎቻችን በእግዚአብሔር(አላህ) መኖር የምናምንም ሆነ የማናምን፤ የክርስትናን እምነት የተቀበልንም ሆነ ያልተቀበልን፤ በሙሴ የነፃነት ተጋድሎና በየሱስ ፍትሐዊነት ብዙ እንከራከራለን ብየ አላስብም። እነዚህን ሃይማኖት የተመሰረተባቸዉን አለቶች በፈጠራ ታሪክ ተዋናዊነት የሚመድቧቸው "ቁስ-አካላዊ" ነን የሚሉት እንኳን ሙሴና እየሱስ የተናገሩት ወይም የሰሩት ትክክል አልነበረም ሲሉ በበኩሌ ሰምቼ አላዉቅም። ከአባይ ወንዝ በደንገል ተጠቅሎ በፈርኦን እህት አማካኝነት የተገኘዉ ሙሴ (ሙሴ = ከዉኃ ዉስጥ የውጣ) ዘጸአት ፪:፲ {1} ያደገዉ በፈርኦን ቤተ-መንግስት ነበር። ነፍስ እያወቀ ሲመጣ ፈርኦን በእስራኤላዊያን ላይ የሚፈፅመዉን አድሎአዊ ያስተዳደር በደል ሲመለከት የቤተ-መንግስቱን የድሎት ኑሮ እርግፍ አድርጎ ለመተው ወሰነ። ለፍትሕ ሲል ጉረሮዉን ለጥማት፣ ሆዱን ለርሃብ፣ ቆዳዉን ለርዛት አሳልፎ ሰጠ። ፈርኦን በባርነት ከሚገዛቸው፣ ከሚገላቸው፣ ከሚገርፋቸውና ከሚያሳድዳቸው የእግዚአብሔር ልጆች ጋር አብሮ ቆመ። መብል መጠጡ የተትረፈረፈብትን፤ ስጋጃ የተነጠፈበትን አለም ትቶ ምርኩዙን አንጥልጥሎ በበርሃ ተጓዘ። ሕዝቡንም ወንድ የሆነ ሂብሩ ህፃን ልጅ በመግደል ወይም በማስገደል ከታወቀዉ አረመኔው ፈርኦን መንጋጋ በእግዚአብሔር ፈቃድ አላቀቀ። {1} ነፃም አወጣቸው። ሙሴም እንኳን የሰዉን የልብ፤ የመለኮትን መስኮት አስከፍቶ ከእግዚያብሔር በቀጥታ ለመነጋገር ቻለ። በሰዉ ልጅ ዘንድም ይኸው ከአጥናፍ አጥናፍ በደግ ስራዉ ይነሳል። አምስቱ መጻሕፍቱ ይነበባሉ። ብዙ ሰዉም ልጁን በርሱ ስም ይሰይማል። ይኸንን አስተዉሎ አሁን ባገራችን ያለዉን ሁኔታ ያገናዝቧል። ከቀርብ ጊዜ ወዲህ ያሉ የኛ የቤተ-ክህነት ሰዎች ያማረ ካባቸውን ደርበው፣ "የተዋበ" ቆባቸዉን ግጥም አርገው የሙሴን መጻሕፍት በመጥቀስ የሚስተካከላቸው የለም። ነገር ግን እርሱን እንደ አርያ ወስደው እንኳን ነፃ ሊያውጡን እንደበሬ አፍነው "እኛ ያልነዉን ብቻ ተቀበሉ!" ከሚሉ ገዥዎቻችን ጋር አብረው ያሹናል። እንደ ገብስ ያፍተለትሉናል፤ እንደላምም ያልቡናል። እንዲያም ሲል ያሳስሩናል፤ ያይን ብረታቸዉ እያየ ያስገድሉናልም። እጃቸዉን ግን ለስለት መይም ላስራት ካስገባነዉ መዋ አያነሱም። ታዲያ ይህ በድንጋዮች ማለቅ የተጋለጠውን ትንሽ ጠጠር ማናገር ይነሰው?

እንደ ሙሴ ሁሉ በእየሱስ ክርስቶስ አምላክነት የምናምንም ሆነ የማናምን ባስተላለፋቸዉ መልእክቶችና ሰራቸዉ በተባሉት ሥራዎች በጎነት ክርክር ዉስጥ የምንገባ አይመስለኝም። በወቅቱ ሕግን እያነበነቡ ነገር ግን የማይፈጽሙ ፈሪሳዉያን በሌላ በኩል ደግሞ የሮማዉ ንጉስ አዉግስቶስ ቄሳርን ወክሎ እየሩሳሌምን ያስተዳድር

የነበረዉ ሄሮድስ ተሰሚነቱን ስልፈሩት ሁለቱም ወገን ተስማምተዉ በተሸከመው ግንድ ወስደዉ ሰቀሉት። {2,3}. እርሱ ግን ወቅቱ ለተመቻቸው ለሁለቱም ወገን ክንዳሞች ሳያጎበድድ ህይወቱን አሳልፎ ሰጠ። በደሙ የዋጀው እምነትና ስሙ ግን በአለንባት ምድር ከተስፋፉ ይኸው አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ዘመን ተቆጠረ። ሳይነጋ ሶስቴ እየሱስን የከዳዉ ስምኦን ጴጥሮስ እንኳን እየሱስ ከሞተ በኋላ የበለጠ በእምነቱ ፀንቶ እየወደቀ እየተነሳ የክርስትና እምነትን በሮም አለት ላይ ተከለ። {6,7} ዳሩ ግን እርሱም በበጎ ስራዉ ምክንያት ተገደለ። እንዲያዉም እየሱስ ራሱ ወደ ላይ ሆኖ ስለተሰቀለ ከሱ ላለመወዳደር ሲል ራሱን ወደ ታች ዘቅዝቀዉ እንዲገሉት ስለጠየቃቸው ታርዶ እደሚገፈፍ በግ ዘቅዝቀዉን ነው የገደሉት እየተባለ ይነገራል። {6,8}. ሐዋርያዉ ጳዉሎስም እንደዚሁ ለህዝብ በሰበከዉ እምነትና በበጎ ስራዉ ምክንያት ከአንገቱ ላይ ተቆርጦ ተጣለ። {6, 8} ቅዱስ ጴጥሮስም ሆነ ቅዱስ ጳዉሎስ በሰዉነት የማይቀረዉን ሞት ሞተዋል። ሰው ባካል ያላዩውን የሰማዩን ጽድቅ እንኳ ብንተወዉ በምድር መጽደቃቸዉን ማየት የሚሳነዉ ያለ አይመስለኝም። ቤተ-ክርስቲያኑ፣ ሰዉ ፣ ከተማው፣ መንገዱ፣ አንዳድ አካባቢ እንሰሳው ሁሉ ሳይቀር በነሱ ስም ይሰየማል። ልጁን በይሁዳ ስም የሰየመ ክርስትያን በተለይም ኢትዮጵያዊ እስካሁን አልሰማሁም። የሚያሳዝነዉ ዛሬ በጎቻቸውን በቀበሮ የሚያስነጥቁ፤ በማጭበርበርና በማታለልም ቆዳቸዉን እየገፈፉ የሚበሉ ልግመኛ እረኞችም በእኒያ እየሰሱስ በመረጣቸው ሐዋርያትና ሰማእታት ስም እየተሰውየሙ ቅዱስ ስማቸዉን ማርከሳቸው ነው። ምእመናን፣ የስራ ባልደረባ የሆኑት ማተባቸዉን ያልቆረጡ ካህናት በእመነታቸው ምክንያት ብቻ እንኳን ሲሞቱ እንኳን ገዳይን ሊገስፁ ለሞቱት ጸሎት ማድረስም ይከብዳቸዋል። ከሚያልቀው ህይወት ሁሉ የነሱ ጉርስ፤ የሚተኙበት አልጋ የሚንፈላሰሱበት መኪና ይበልጣል።

እነ ጳዉሎስን የተኩ አቡን እየተባሉ የሚሾሙት ጳጳሳት አስፈላጊነት የእየሱስን ወረድ ብሎም የጴጥሮስ፣ የጳዉሎስንና መሰል ሐዋርያትን ስራ በቀጣይነት ካለማመንታት፤ ስጋቸዉ ሳያሸንፋቸዉ እምነትን እንዲያስፋፉ በጎቻቸዉን እንዲጠብቁ ነበር። በርግጥም አንዳድ ትጉህ የሆኑ፣ ለመስቅልና ለማተባቸው የተገዙ አልጠፉም። ወደ ሁኋላ ሄደን ብዙም ሳንርቅ የግብፁን አቡነ ሽኖዳና የእኛዎቹን ሰማእታት አቡነ ጴጥሮስናን አቡነ ቴዎፍሎስን ለእነዚህ ምሳሌዎች ይሆኑናል።

የግብፅ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን መቶ አስራ ሰባተኛው ጳጳስ የሆኑት አቡነ ሽኖዳ የክርስትናን ሃይማኖት ሕዝባቸዉ በሄደበት ያለም ክፍል በማስፋፋት የታወቁ ብፁእ አባት ናቸው። ከዚህ አልፎ ክርስቲያኖች ግፍ ሲፈፀምባቸው እኔን መጀመሪያ ግደሉኝ ብለው ከፊት የሚገኙ ለመሆናቸው እንኳን በጎች ቀበሮዎችም ይመሰክሩላቸዋል። ለበጎቻቸው ትጉህ እረኛ ሆነው በመቆማቸው እ.ኤ.አ በመስከረም 1981 አንዋር ሳዳት ከቦታቸው አባረራቸው። {8} አቡነ ሽኖዳ በጎቻቸዉን ለቀበሮ በመገበር ድሎታቸዉን ለመጠበቅ በመቅቡጥ አልተደለሉም። ለሳዳት ክርንም አላጎበደዱም። በጎቼን ቀበሮና ተኩላ ሲበላቸው ከማይ እኔኑ የግብፅ በርሃ አቃጥሎ ይግደለኝ ብለው ወደ በርሃ መነኑ። ለስጋቸዉ ቢሳሱ ኖሮ ምድራዊ አለቃቸዉ ያላቸዉን ተቀብለው ጥይት እማይበሳው መኪና እየነዱ፣ አባቱ ነኝ ከሚሉት ምእመናን እየተደበቁ፤ በጠበደሉ ወታደሮች እየተጠበቁ እልፍኝና አዳራሽ እየቀያየሩ፤ እንደ ሕጻን ልጅ ጉንጭ ትምክ ከሚል ፍራሽ ላይ እየተንፏለሉ መኖር በቻሉ ነበር። ሌላው ከሰማእታት የሚያመሳስላቸው ደግሞ የተሰደዱት ዋሽንግተን ዲሲ ወይም ለንደን አለመሆኑ ነው። ምግም ሆነ ዉሀ ከማይግኝበት እንደሳት ከሚያነድ አሸዋማ የግብፅ በርሃ ዉስጥ አምላካቸዉን ተማምነው ሄዱ፤ ነጎዱ። {8} አዎ አብርሃምም፣ ሙሴም፣ እየሱስም ከናቱ ጋር የተሰደዱት ወደ በርሃ ነበር። ያባረራቸዉ አንዋር ሳድት ዛሬ የለም። እርሳቸዉ ግን ዛሬም የኢትዮጵያን ቤተ-ክርስትያን አንድ አስራኛ የሚሆን አባል የሌላትን የግብፅ ቤተ-ክርስትያን እንደቀደምቶቻቸው ሁሉ ባለም ትልቅ መድረክ ላይ ተክለዋት ይገኛሉ። ይኸዉ እንደኔ አይነቱንም እየማረኩ እንዲፅፍላቸዉ ያደርጋሉ። ስማቸዉም እንደ ሐዋርያዉ ጴጥሮስ ሁሉ ባለት ላይ ተፅፏል። እስከ ዘላለምም ይነበባል። ይህ በጎ ሥራቸዉ እስካለም መጨረሻ እንደሚነሳ ጥርጥር የለኝም። ታዲያ ይኸንን አዉቆ አሁን በተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን ያለውን የሞራል ቀውስ ያስተዋለ ጠጠር እንዴት አይዘን? ነገ ለምንተወው ምድራዊ አለም ካህን የነፍስ ልጁን ለተኩላ ገፀ-በረከት ማቅረቡን የተገነዘበ ጫጩት ድንጋይ ምነው አይናገር?

ጥቁሩ ቆዳቸዉ ሸፍኗቸው የስራቸዉን ያህል ስማቸው ባለም ላይ አልዋለም እንጅ ፋጣሪ ምስጋና ይግባዉና እኛም



ሐዋርያትና ሰማእታት ነበሩን። አካለቸው ቢለየን መንፈሳቸው ዛሬም አብሮን ነዉ። ምናልባት መኖራቸዉ አልታወቀ ብሎ እንጅ ዛሬም በየገዳማቱ በጸሎት የሚማፀኑልን አባቶች አሉን ብየም አስባለሁ። አገራችን በግፈኛው መሶሎኒ በተወረረችበት ወቅት እንደሙሴ ዘንጋቸዉን ይዘዉ ነፃ ሊያወጡን የተነሱ እቡነ ጴጥሮስ የሚባሉ የበቁ አባት ነበሩን። ሙሴ የፈርኦንን እብሪት ከምንም እንዳልቆጠረው ሁሉ አባታችን

ጴጥሮስም የመሰሎኒኒ ባለሚሎች ዛቻ ከቁብ ሳይቆጥሩ ለሕዝባቸው ባደባባይ ጸለዩ፤ ታገሉ። ፋሽሽት አርፈው እንዲቀመጡ አለበለዚያ ሊገላቸውም እንደሚችል የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ሲሰጣቸዉም “የአገሬን ሕዝብ በመርዝ ጋዝና በቦንብ ስትፈጅዉ የሚያሰማው ጩኸት ሀሌናየን እንዴት ብሎ እረፍት ይሰጠዋል?” ብለው ከኢሳያስ መጽሐፍ የሚከተለዉን ጠቀሱ። ኢስ ፶፩፥ ፯ *“ጽድቅን የምታዉቁ ሕጌም በልባችሁ ያለ ሕዝብም ሆይ ስሙኝ፤ የሰዉ ተግዳሮት አትፍሩ፤ በስድባቸዉም አትደንግጡ። እንደ ልብስም ብል ይበላቸዋል። እንደበግ ጠጉርም ትል ይበላቸዋል። ጽድቄ ግን ለዘላለም ማዳኔም ለትዉልድ ሁሉ ይሆናል።”* {8} አዎ እርሳቸው እንዳሉት ፋሽሽትን ትልም ብልም በላዉ። በእንደነሳቸው አይነት አባቶቻችን መሰዋእትነት ይኸው የነሱ ትዉልድ እኔን ጨምሮ ከቅኝ አገዛዝ መከራ ድነናል። በዚህም ምክንያት ዛሬ በመላዉ አለም በችግር፣ በርሃብና በበሽታ በምንታወቅበት ዘመን እንኳን ደረታችንን እንደ ጭድ ክምር ወደ ላይ እየነፋን “ማን ከኔ ተስተካክሎ” በሚል መንፈስ እጃችንን በኪሳችን እየከተትን እንጀነናለን። ግዳይ እንደጣለ ጀግና እንጎማለላለን። ታዲያ ይህ ሁሉ የብፁኡ የአቡነ ጴጥሮስና የመሰሎቻቸዉ መንፈስ ሳይሆን ይቀራል? ሰማእቱ አባታችን የሚወዱትን አገራቸዉና የነፍስ ልጅ የሆነዉን መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመጨረሻ ጊዜ በአረመኔው ፋሽሽት የቅስፈት ሐይል ሲለዩም “ *የፋሽስቱን የወረራ ሐይል እንዲመልስ እግዚያብሔር ሆይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብርታቱንና ጥንካሬዉን ስጠው!”* ብለው መስቅላቸዉን ባራቱም አቅጣጫ አማትበዉ ጸለዩ። በመቀጠልም “ *የኢትዮጵያ ምድርም ለፋሽሽት አትገዛ”* ብለው ገዘቱ። {7,9} እግዚያብሔር ጸሎታቸውን ሰማ፤ የሕዝቡን ክንድ ከዳር እስከዳር አበረታላቸው። አጠነጠነው። ፋሽሽትንም መግቢያ መድረሻ አሳጣው። ደቆሰው። ምድሩም የተባለውን አደረገ። ተራራው፤ ጫካዉ፤ ዳገቱ፤ ቁልቁለቱ ከፋኖው ተወዳጀ። ለፍትህ ታጋዩ እንደጋሻ ሆነ። ወንዞችና ሐይቆች ጀግኖችን አጠጡ። ፋሽሽትና ባንዳዉን ደግሞ ዋጡ። አሰመጡ። አቡነ ጴጥሮስ ያሉት ሁሉ ሆነ። አበሻ ነፃነቱን ጠበቀ። ምድሩም ለፋሽሽት ሳይገዛ ቀረ። በጴጥሮስ ዘንድ ቃል እዉን ሆነ። በኛ ዉስጥም ሰረፀ። የጴጥሮስ ቃል ገና በልጅ ልጅ ልጆቻችንም ሲሰርፅ ይኖራል። አዎ! ይኖራል፤ ይኖራል …

በተመሳሳይ መንገድ በእውቀታቸው፣ በበዙ ቋንቋ ችሎታቸው፣ በሃይማኖት አባትነታቸውና በትእግስታቸው አያሌ ቋሚ ምስክሮች የሚመሰክሩላቸው አቡነ ቴዎፍሎስ በባእድ ሳይሆን አብረዋቸው በሚጸልዩና በሚያገለግሉ “የቤተ-ክህነት” ሰዎችና ሌሎችም ተንኮለኞች አነሳሽነት አገር በቀል በሆነ ፋሽሽት ተገለዋል። አቡነ ቴዎፍሎስ ለወቅቱ ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱም በጣም አርቆ አሳቢ ስለነበሩ ይህ የዛሬው ጉዳይ እንደሚመጣ ታይቷቸው ቤተ-



ክርስቲያኑዋ ከሲሶ መሬት ተላቃ በራሷ እንድትተዳደር ለማድረግ ያለደረጉት ጥረት እንዳልነበረ ብዙዎች ይመሰክራሉ። የቤተ-ክህነትን ትምህርት ጥራት ለመጠበቅና ከዘመኑ ጥብብ ጋር ለማዛመድም ብዙ ትግል እንዳደርጉ ይወሳል። ቤተክርስትያኗን ባለም መድረክ ከፍ ብላ እንድትታይ ማድረጋቸውም ጥርጥር የለዉም። {7} እንዲያዉም ሌሎች እህቶች የሆኑ ቤተክርስትያናት እስካሁን ድረስ በኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን አባትነት በፀሎት ጊዜ የሚያስታዉሷቸው እርሳቸውን ነው ይባላል። አቡነ ቴዎፍሎስን እንደፈለገው ሊያሽከረክረቸው ያልቻለው፤ የአምላክን መኖር የካደ አገር በቀል አጥፊ እርሳቸውንም እንደ ጴጥሮስ ቀጫቸው። እንደዛሬዎቹ አንዳንድ ጳጳሳት ገዳዮች ሲዘፍኑ አብረው ለመዝፈን ፈቃደኛ ቢሆኑ ኖሮ በእስር ቤት ተንገላተው፣ እግር ተወርች ታስረው ባልተገደሉ ነበር። በሰዉነታቸው ሊያመልጡት የማይችሉትን የስጋ ሞት በሌላ ሰው እጅ አጥተዋል። ስማቸው ግን እንደ ሐዋርያዉ ጴጥሮስ ሁሉ ባለት ላይ ተቀርፏል። ሲነበብም ይኖራል።

እንግዲህ ያለፉትን ሰማእታት አነሳሳን። የሙሴንና የእየሱስን ስቃይና መከራ፣ የሐዋርያቱን ጳውሎስና ጴጥሮስን እሚሚት፤ የሽኖዳን ትግል፣ የሰማእታቱን ጴጥሮሰ- ዘኢቶጵያና አቡነ-ቴዎፍሎስን ታጋድሎና ሞት በማንኪያ ጨልፈንም ቢሆን አዋሳን። ይኸንን ላፍታም ቢሆን ከቃኘን በኋላ እንደኔ ከሆናችሁ በአእምሯችሁ የሚጉላላው “ዛሬስ ማን አለን ነው?” በአሁኑ ሰዓት እንደጴጥሮስ ለፋሽሽቶች እንዳይገዛ የኢትዮጵያን ሕዝብ ክንድ አጠንክር ብሎ የሚፀልይ አባት አለን ወይ ነው? መልስ ካላችሁ ንገሩኝ። እኔ እንደሁ ላመታት ይኸንን ጥያቄ ራሴን ደጋግሜ ጠይቄ ያገኘሁት መልስ “ጽድቁ ቀረቶ ባግባቡ በኮነነኝ” የሚል ነው። ብዙዎቻችሁም መልስ አጥታችሁ በሆደ ባሻነት፤ በትካዜና በምሬት መሬት የምትጭሩ ይመስለኛል። በዚች ወቅት እንኳን ለዘመናት በፍቅር አብረው የኖሩ ወገኖቻችን ባለማወቅ በሃይማኖት ሰበብ እርስ በርሳቸው በመተላለቅ ላይ ይገኛሉ። የሃይማኖት አባት ነን የሚሉት ግን ሚቾቹ ባስገቡት የአስራትና ስለት ገንዘብ በተገዛ፤ ቆንጨራም ሆነ ጥይት በማይበሰው ዙፋን ያለው አዉቶሞቢል ዉስጥ ተቀምጠው በመንፈስ-ቅዱስ ሳይሆን እንደ ኮርማ በሚቀለቡ ወታደሮች እየተጠበቁ ይኖራሉ። ይህ የማያሳዝነው፣ የማያስተክዘውና የማያስቆዝመው ካለ ታድሏል።

እንደ ጥንቱ እንደ ጥኋቱ ከቤተ-ክርስቲያን መሪዎች እጅ ፀበል መፍሰስ ሲገባው ዛሬ ግን በጳጉሜና በጥምቀት ሳይቀር የጎሸ ውኃ ይንፏፏል። እንኳን ከነፍስ አባት እጅ ከምድር የሚፈልቅ የጎሸ ዉኃም ለሰው ልጅ ጠንቅ ነው። እኛ እንደሁ ሞኞች ነን። የቤተ-ክርስትያን መሪዎች የነፈጉንን ምህረት ነፍጥ ያነገበ ገዥ ባለመስጠቱ እንወቅሰዋለን። መስቀልን የጨበጡ፣ ቆብን ያጠለቁ ከእዉነት ሲለያዩ እነ ሕይወት-ኳሱን ቀጠፉ ብለን እናማቸዋለን። አቡንና ጳጳስ ለማይመጥኑት ወንበር ሲሽቀዳደሙ እያየን ሌሎች የማይገባቸዉን ወንበር በመንጋጋቸው ነግንገው ያዙ ብለን ቆሽታችን ድብን ይላል። “ያሳ ግማቱ ካናቱ” ይላል ተረት የማያልቅበት ያገሬ ሰው። ችግራችን ከላይ ነው። አዎ ከላይ! ከላይ አላግባብ ከተሰቀለው “ቆብ”! እንደጴጥሮስ አይነት ቃልን ከስጋቸው ያዋሃዱ ሁለት ሶስት የሃይማኖት አባቶች ቢኖሩን የንፁሐን ደም ጠብ ሳይል ችግራችን በጊዜ በተፈታ ነበር። እንደ አለመታደል ሆኖ ጴጥሮስም ሆኑ ቴዎፍሎስ ተመልሰው  መጥተው ውኃን ገና አልባረኩም። ውኃዉም ገና ጸበል አልሆነም። እኛም ገና አልተጠመቅንም። ሐጥያታችንም ገና አልጸዳም። በሥጋም ሆነ በነፍስ ለመዳን የየሱስን ፈለግ በመከተል ለበጎቻቸው ልእልና ሲሉ የመከራን ጽዋ የጠጡትን፣ ህይወታቸውን አሳልፈው የሰጡትን የጴጥሮስንና የቴዎፍሎስን አይነት ትጉሐን እረኞች ተርበናል። ከእጃቸው ድፍርስ ውኃ ሳይሆን ጸበል የሚያፈልቁ የነፍስ አባቶችን  ተጠምተናል።  ርሃቡን ያስታግስልን። ጥማታችንን ይቁረጥልን! አሜን።

*ዋቢ*


1. *ኦሪት ዘጸአት*
2. *የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ ፳፫*
3. *የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፱*
4. *የሐዋርያው የጴጥሮስ መልእክት*
5. *የሐዋርያው ጳዉሎስ መልእክቶች*
6. *ነገር ሃይማኖትና ሥልጣነ መንግስት በሮማ ግዛት (ዳዊት ብርሃኑ)*
7. *ጴጥሮስ በዚያች ሰዓት (ሎሬት ጸጋዬ ገብረ-መድህን)*
8. *The free encyclopedia*
9. *Fesseha Mekuria and SVen Rubenson: A Short life history of martyr bishop Abune Petros who became martyr on the 29th of July 1936, in Addis Ababa Ethiopia in the struggle against colonialism and oppression.*



**በላይነህ አባት** (abatebelai@yahoo.com)
**ህዳር ፲፱፻፺፱ ዓ.ም**